# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 229 መስከረም 24 2005 ገጽ 1


የግንቦት 7 ዓላማ ወያኔን በማስገደድ ወይም በማስወገድ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቱ የተከበረበት፤ የኢኮኖሚ ብልፅግናና ማኅበራዊ ፍትህ የሚገኝበት፤ የዜጎች ሕይወት፣ ደህንነትና ጥቅም የተከበረበት እና የሕዝቧ አንድነትና ትስስር የጠነከረበት ሃገር እንዲኖረው ማድረግ ነው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

# የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ለወያኔ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ሰጡ

በሚሊዮን የሚቆጠሩ የሙስሊም እምነት ተከታይ ወገኖቻችን በትናትናው ዕለት ዓርብ መስከረም 25 ቀን በአገሪቱ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ከተሞች ተቃውሞአቸውን ለማሰማት በሰላማዊ መንገድ ወጥተው ከነርሱ ፈቃድ ውጪ የእምነቱን መሪዎች በየቀበለው ለማስመረጥ የሚደረገው ጥረት የከፋ መዘዝ ሊያስከትል እንደሚችል ለማስገንዘብ ለዘረኛውና አምባገነኑ ወያኔ አገዛዝ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ቢጫ ካርድ ማሳየታቸውን የግንቦት 7 ዘጋቢ አጠናክሮ ከላከልን ዜና ለመረዳት ተችሎአል።

በአገራችን ውስጥ በአይነቱ የመጀመሪያ በሆነው በዚህ ታላቅ ትንግርታዊ የተቃውሞ ሥነሥርዓት ላይ አዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው አንዋር መስጊድ ብቻ ቁጥሩ ከግማሽ ሚሊዮን ያላነሰ ሕዝብ ተገኝቷል ተብሎአል። ቢጫ ካርድ የማሳየት ሥነሥርዓት የተካሄደው ከጅሙዓ ሶላት በኋላ ሲሆን በርካታ የተቃውሞ መፈክሮችም ሲደመጡ ውለዋል። የሙስሊሙ ህብረተሰብ ላለፉት 11 ወራት እያካሄደ ባለው የሙብት ጥያቄ የዚህ አይነት የከረረ ተቃውሞ አሰምቶ እንደማያውቅ የዘገበው ዘጋቢያችን፤ በጊዜያዊነት የተመረጡ የመፍተሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት በታሰሩበትና ከፍተኛ ወከባ በሙስሊሙ ላይ እየተፈጸመ ባለበት በአሁኑ ሰዓት ይህ በሃይል እንዲካሄድ የታሰበው ምርጫ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል እንዳበሳጨና ውስጥ ለውስጥ በተደረገ ግንኙነት አብዛኛው ተሳታፊ ቢጫ ጨርቅ ይዞ በመውጣት ተቃውሞው በተካሄደባቸው ከተሞች የሚገኙትን የአገዛዙን ሹሞችና ካድሬዎች አንገት ሲያስደፋ እንደዋለ ለማወቅ ተችሎአል። በዚህም የተነሳ አዲስ አበባችን ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የሚሆን ህዝብ ይዞት በወጣው ቢጫ ካርድ ተጥለቅልቃ ውላለች።

ከአዲስ አበባ ወጪ ለወያኔ የቢጫ ማስጠንቀቂያ ካርድ የሰጡ ከተሞች ደሴ፣ ከሚሴ፣ ሻሸመኔ፣ አዳማ፣ ወልቂጤ፣ ጅማ፤ በደሌ እና ሌሎችም በርካታ የኢትዮጵያ ከተሞች እንደሆኑ የዘገበው ዘጋቢያችን የክርስቲያኑ ህብረተሰብ በሙስሊም ወንድሞቹ ድፍረትና ወኔ እጅግ ከመደሰት አልፎ " ሙስሊም ወገኖቻችን አኩርተውናል " እያለ መሆኑን ገልጾአል።

አዲስ አበባ ውስጥ በአንዋር መስግዱ የተደረገውን ተቃውሞ የተከታተለው የግንቦት 7 ዘጋቢ ያነጋገራቸው አቶ ሃምዛ ሸምሱ የሚባሉ የ75 ዓመት አዛውትና የ11 ልጆች አባት "እኔ በኢትዮጵያዊነቴና በሙስሊምነቴ እንደዛሬ የኮራሁበት ቀን የለም" በማለት ምክንያታቸውን ሲያስረዱ "ቢጫ ካርድ የምናውቀው በኳስ ሜዳ ነበር። እሱን በቴሌቪዥን እንጂ እኔ ኳስ ሜዳ ሄጄም አላውቅም። ዛሬ ግን እኔ የ70 ዓመቱ ሽማግሌ መንግሥትን 'ተጠንቀቅ' ለማለት አላህ አበቃኝ። አላሁ አክበር። ከእንግዲህ ኢህዴግ ለራሱ ሲል ይወቅ። እንቢ ካለ በላ ይወርድበታል። አላሁ አክበር" በማለት የደስታ ሲቃ እየተናነቃቸው አስተያየታቸውን ሰጥተውታል።

ወጣት መሃመድ ተማም ደግሞ "መንግሥት ድምፃችን ይስማ!!!! ጮኸን፣ ጮኸን ካልተሰማን የሚከተለውን መገመት እኮ ቀላል ነው። እኔ ለዲኔ ሕይወቴን ለመስጠት ዝግጁ ነኝ" ብላል።

ወይዘሮ ዘይነባ ከዲር ደግሞ "እኔ ቢጫ ካርድ ያወጣሁት በመጀመሪያ ደረጃ ለኢቲቪ ነው። በአላህ ይዘናችኋል ኢትቪዎች አትስደቡን!!! አትዋሹ!!! ሰለቸን" ብለዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)



## ነፃነትና ገለልተኛ የምርጫ አስፈፃሚ ተቋማት በሌሉበት ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ሊኖር አይችልም!!!

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ከዚህ በፊት ሲያደርገው እንደነበረው ሁሉ የሴራ ምርጫ አዘጋጅቶ በኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ትግል ውስጥ ውሃ ሊቸልስ ተዘጋጅቷል።

እንደ እቅዱ ከሆነ አገዛዙ በሚቆጣጠረው የሴራ ምርጫ አማካይነት ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ የካድሬ መሪዎች ሊመረጥ ነው። ምርጫውን ተከትለው ስለሚመጡ ነገሮችም መገመት ከባድ አይደለም። እንደተለመደው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ራድዮ ስለ ምርጫው ህጋዊነትና ፍትሃዊነት ተግተው ይደሰኩራሉ። ቀጥሎም አዲሱ አመራር በቀድሞው መጅሊስ የተጀመሩትን ወያኔያዊ ፀረ-ሕዝብና ፀረ-ኢትዮጵያ ተግባራት ለማስቀጠል ቃል ገብቶ ሥራውን ይጀምራል። በአዲሱ የመጅሊስ አመራር ከለላ ወያኔ በሙስሊሙ ላይ የሚያደርሰውን አፈና፣ እስርና እንግልት አጠናክሮ ይቀጥላል።

የሴራ ምርጫዎች የአምባገነኖች መሣሪያዎች ናቸው። መስከረም 27 ቀን 2005 ዓ.ም. ሊደረግ የታቀደው የሙስሊም አመራሮች ምርጫም ከዚህ ቀደም በወያኔ አስፈፃሚነት ሲደረጉ እንደነበሩ ምርጫዎች ሁሉ የሴራ ምርጫ ነው፤ ዓላማውም አምባገነንነትን ማጽናት ነው። ለምርጫው እየተደረጉ ያሉት ዝግጅቶችም የሚያመለክቱት ይህንኑ ሃቅ ነው።

- ወያኔ ካድሬዎቹን በምርጫ አስፈፃሚነት መድቧል፤
- የምርጫው ታዛቢዎችም የወያኔ ካድሬዎች ናቸው፤
- ለቁጥጥር እንዲያመችም ምርጫው የሚካሄደው በቀበሌዎች ነው፤
  ሙስሊሙ ባይወድም በግድ እንዲመርጥ እየተገደደ ነው።

በዚህ ሁኔታ የሚፈፀም ምርጫ ነፃ፣ ፍትሃዊና ተዓማኒን ሊሆን ፈጽሞ አይችልም።

ብዙሃኑ የሙስሊም ማኅበረሰብ ይህንን የሴራ ምርጫ በመቃወም ድምጹን ያሰማ ቢሆንም ሰሚ አላገኘም። ሙስሊም ወንድሞቻችንና እህቶቻችን የምርጫ ካርድ ባለመውሰድ ተቃውሞዓቸውን ቢገልጹም ወያኔ በቀበሌም በእድርም እያስገደደ ጥቂት ካርዶችን በትኗል። የቀረው ቀኑ ሲደርስ ቁጥሮችን በፎርም ሞልቶ ሊሾማቸው የሚፈልጋቸውን ሰዎች "ተመረጡ" ብሎ ማሳወቅ ነው።

የወያኔን የሴራ ምርጫ ተውኔት ኢትዮጵያዊያን በተደጋጋሚ የተመለከትነው በመሆኑ ሰልችቶናል። ወያኔ ሥልጣንን በጉልበቱ ከያዘ ጊዜ ጀምሮ በርካታ የሴራ ምርጫዎችን አይተናል። በመጠኑም ቢሆን ከሌሎቹ የተሻለ የነበረው የ1997ቱ ምርጫም እንደምን ባለ አሳዛኝ ሁኔታ እንደተጠናቀቀ ሁላችንም የምናውቀው ነው።

በግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እምነት ወያኔ በሥልጣን ላይ እያለ እና እሱ እየተቀጣጠረው የሚደረግ ምርጫ እውነተኛ የሕዝብ ፍላጎት የሚገለጽበት ነፃ፣ ፍትሃዊና ተዓማኒን ሊሆን አይችልም። በወያኔ አስተባባሪነትና አስፈፃሚነት የሚደረጉ ምርጫዎች ሁሉ የሴራ ምርጫዎች ናቸው። የሴራ ምርጫዎች ዓላማ ለአንባገንነት ሽፋን መስጠት ነው።

እውነኛ፣ ነፃ፣ ፍትሃዊና ተቀባይነት ያለው ምርጫ እንዲኖር ሕዝብ ሃሳቡን በነፃ የሚገልጽበት ሥርዓት መገንባት ይኖርበታል፤ እንዲሁም ምርጫውን የማስፈፀም ብቃት ያላቸው ገለልተኛ ተቋማት ሊኖሩ ይገባል። ነፃነትና ገለልተኛ ተቋማት በሌሉበት ሁኔታ የሚደረግ ማናቸው ምርጫ ነፃ፣ ፍትሃዊና ተቀባይነት ያለው ሊሆን አይችልም። ስለሆነም መስከረም 27 ቀን 2005 ዓም በቀበሌዎች የሚደረገው የሙስሊሙ ማኅበረሰብ መሪዎች ምርጫ ተቀባይነት የለውም።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በምርጫ ስም በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ላይ የሚጫንበትን አገዛዝ በጽኑ ይቃወማል። የእምነት ብቻ ሳይሆን ሰብዓዊ መብቶች ሁሉ የተከበሩባት እና እኩልነት የሰፈነባት ኢትዮጵያ እንድትኖረን የወያኔን የሴራ ምርጫዎችን ማክሸፍ ይኖርብናል ብሎ ያምናል። ግንቦት 7 የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የሚያደርጉትን የመብት ማስከበር ትግል ይደግፋል፤ የክርስትያኑ ማኅበረሰብም በዚህ የመብት ጥያቄ ከሙስሊም ወንድሞቹና እህቶቹ ጎን እንዲቆም ጥሪ ያደርጋል።

የግንቦት 7 ዓላማ ወያኔን በማስገደድ ወይም በማስወገድ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቱ የተከበረበት፤ የኢኮኖሚ ብልፅግናና ማኅበራዊ ፍትህ የሚገኝበት፤ የዜጎች ሕይወት፣ ደህንነትና ጥቅም የተከበረበት እና የሕዝቧ አንድነትና ትስስር የጠነከረበት ሃገር እንዲኖረው ማድረግ ነው።

ለዚህ ክቡር ዓላማ የሃይማኖት ድንበር ሳይከልለን ሁላችንም በአንድነት እንነሳ!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!**

---

## ከመስከረም 20 ጀምሮ ለአራት ቀናት በዝግ የተካሄደው የኦህዴድ ስብሰባ ከፍተኛ ፍጭት የተካሄደበትና በርካታ ነባር አባላት ከድርጅቱ ሊባረሩ የሚችሉበት ሊሆን እንደሚችል ምንጮች ገለጹ

ዘረኛው መለስ ዜናዊ ከዚህ አለም በሞት ከተለየ ወዲህ በህወሃትና ህወሃት በአምሳሉ በፈጠራቸው ድርጅቶች ውስጥ ጥርጣሬና አለመተማመን መስፈኑን በዚህም ምክንያት በተለይ ህወሃትና ኦህዴድ በስብሰባ መወጠራቸውን ከታማኝ ምንጮች የደረሱን መረጃዎች አመለከቱ።

ከመስከረም 20 ጀምሮ በዝግ ስብሰባ የተካሄደውን የኦህዴድ ከፍተኛ አመራር ስብሰባ የመራው ኩማ ደመቅሳ እንደሆነ የገለጹት ምንጮች ግለሰቡ በአብዛኛው የድርጅቱ አባል ዘንድ የማይወደድ እንደሆነና ሰሞኑን ሲካሄድ በነበረው የግምገማ ተቀናቃኞቹን ለማስመታት ትልቅ ተጋድሎ ሲያደርግ እንደሰነበተ ይናገራሉ።

አብዛኛው የኦህዴድ አመራር በበረከት ስምን አንጋሽነት ለጠቅላይ ምንስትርነትና ምክትል ጠቅላይ ምንስትርነት በተሰየሙ ሰዎች ላይ ከፍተኛ ቅሬታ እንዳለው ይታወቃል። በዚህም ምክንያት የሰሞኑ ስብሰባ በረከት ስምን ጥርስ የነከሰባቸውንና እንደተለመደው አንገታቸውን ደፍተው ታዛዥ በመሆን ላለመቀጠል እያቅማሙ ያሉትን የኦህዴድ አባላት ነጥሎ ለመምታት የታለመ ነው ተብሎአል።

በህትመት ሥራው ላይ የበረከት ስምን እጅ እንዳለበት የሚነገርለት ሰንደቅ ጋዜጣ የሰሞኑን የኦህዴድ ስብሰባ ሲዘግብ ስብሰባው የኦህዴድን መስመር በርዘው በሚንቀሳቀሱ አመራሮች ላይ የማያዳግም እርምጃ ለመወሰድ የሰላ የመደብ ትግል የተካሄደበት እንደነበር ገልጾአል።

ሰንደቅ ላይ የወጣውን ዘገባ የተመለከቱና ለአገዛዙ ቅርበት ያላቸው ምንጮች እንደገለጹት አብዛኞቹ የኦህዴድ አባላት በሙስና የተጨማለቁ ናቸው በሚል ውንጀላና የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑትን ደግሞ በሃይማኖት አክራሪነት ፍረጃ ለመምታት የተቀረውን በኦነግ ሰርጎ ገብነት ለማስወገድ ዝግጅት መጠናቀቁን ይገልጻሉ።

ከመለስ ዜናዊ ሞት ቦኋላ የኦህዴድን አመራር ልብ ያሸፈተው ለጠቅላይ ምንስትርነት በተደረገው ምርጫ ከኦህዴድ ብቁ ሰዎች እጻሉና ቦታው እንደሚገባቸው የህወሀት ተላላኪ ለሆነው ኩማ ደመቅሳና ቡችሎቹ ተነግሮአቸው ወደ ኢህአደግ አመራር ስብሰባ ከሄዱ ቦኋላ የተሰጣቸውን ሃላፊነት ወደ ጎን ትተው መለስ ዜናዊ በህይወት በነበረበት ወቅት ያድርጉ እንደነበረው በረከት ስምን አጭቶ ላቀረባቸው ዕጩዎች አጨብጭበው መመለሳቸው የፈጠረው ብሶት ነው ተብላአል።

## የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ለወያኔ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ሪፓርተራችን ያነጋገራቸው ሰዎች ሁሉ በደስታ ሲቃ ውስጥ ነበሩ። ብዙዎች "ይህ ታላቅ ቀን ነው፤ ይህ ታሪካዊ ቀን ነው" ሲሉ ተደምጠዋል።

የፓለቲካ ተንታኞች የዛሬው እለት ትዕይንት የሙስሊሙ ትግል የደረሰበትን ከፍተኛ ደረጃ ያመለክታል ይላሉ። አንድ ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ ባለሙያ "ከእንግዲህ የሙስሊሙን ትግል የሚገታው ኃይል አይኖርም። ሁላችንም ከዚህ ሃቅ ጋር መታረቅ አለብን። የሙስሊሙን ትግል መደገፍና በአገራችን ውስጥ ለውጥ እንዲመጣ ማድረግ አለብን" ብለዋል።

ዘረኛው አምባገነኑ ወያኔ ግን የሙስሊሙን ጥያቄ ወደ ጎን ገፍቶ በፊታችን እሁድ በሚያካሄደው የይስሙላ ምርጫ ካድሬዎቹን ሊሾም ተዘጋጅቷል። እሁድ አስመራጩም መራጩም ተመራጩም ወያኔ ብቻ የሆነበት ምርጫ ይካሄዳል።

ዘግይቶ በደረሰን ዜና የአፋር ክልላዊ መንግሥት የእሁዱ ምርጫ በመስኪዶች ውስጥ እንዲካሄድ ፈቀደ። ሆኖም ግን ኮሚቴዎቻችን፣ ኡለሞቻችን እና ዱአቶቻችን በእስር ላይ ሆነዉ ምርጫ የማይታሰብ ነዉ ብለዋል። በዓርብ ሶላት በኋላ ይኸው ተቃውሞአቸውን በከባድ ተክቢራ አሰምተዋል። በሀረር ከተማም በታላቁ ኢማን መስጂድ ህገ ወጡን ምርጫ በመቃወም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የከተማዎ ሙስሊሞች ከጁምአ ሰላት ቡሀላ ተቃዉሟቸዉን እንዳሰሙ የደረሰን ዜና ያረጋግጣል።

---

# እኔ እየተከተልኩ እናንተ እየመራችሁኝ !!!

አሁን በቤተ መንግስት ዙሪያ ከሚሽከረከሩ ቡድኖች የምንሰማው ድምጽ “የመለስ ራእይ” የሚል ነው።የመለስ ራእይ “ሳይበረዝ ሳይከለስ” ይፈጸማል የሚለውም አውራ መፈክራቸው ሁኗል።

አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትርም ድምጹን ከፍ አድርጎ እኔ የማስፈጽመው የመለስን ራዕይ ነው ብሎናል።እንግዲህ የራሱ ራእይ ከሌለው ግለሰብ የሚጠበቅ አዲስ ነገር ይኖራል ብሎ ማሰብ ከስህተት ይጥላል።

ኢትዮጵያችን አዲስ ራዕይ ያለውን መሪ ትፈልጋለች።አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር ሃ/ማሪያም ደሳለኝ አሁን ኢትዮጵያ የምትፈልገው ዓይነት መሪ ለመሆን ራሱን ያዘጋጀ አይመስልም።ዘመኑና አገሪቷ የምትፈልገው የራሱ የሆነ አዲስ ራዕይ ያለው ሰው ሆኖ ሳለ የአንድን ዘረኛ ግለሰብ ራዕይ አስፈፅማለው ማለት የአገራችንን ችግር ከማባባስ በቀር የሚፈይደው መልካም ነገር የለም።ሃ/ማሪያም በተሾመ ወይም በተመደበ ግዜ ያደረገው ንግግር ደግሞ ሰውየው ኢትዮጵያን የመሰለች ፈረጀ ብዙ ችግር ያለባትን አገር ለመምራት ራሱን እንዳላዘጋጀ የሚያሳይ ነው።”እኔ እየተከተልኩ እናንተ እየመራችሁኝ” እንዝለቃለን ማለቱ አለመዘጋጀቱን የሚያመለክት ነው።ራሱ መሪ ሁኖ ሳለ ሌላ የሚመራውን የሚፈልግ ኢትዮጵያችንን ከታሰረችበት የዘረኝነት እና የዝሪፊያ ሰንሰለት ያላቅቃታል ብሎ መጠበቅ አዳጋች ነው።

”እናንተ እየመራችሁኝ” የሚለው ትህትና ያለው ንግግር በመምሰሉ ሊያሳስት ይችላል።ይሄ ትህትና አይደለም።ትህትና ሊሆን የሚችለው “እናንተ” የሚለው የኢትዮጵያን ህዝብ ቢሆን ኑሮ ነበር።”እናንተ እየመራችሁኝ” የሚለው ከመጋረጃው ጀርባ የተሰለፉ የሰይጣን ልጆችን ሌሎች እነመለስ ዜናዊዎችን እንጂ የኢትዮጵያን ህዝብ አይደለም።ሌሎች ጨካኞች፤ሌሎች ከእውነት ጋር የማይተዋወቁ ሃሰተኞች፤ሌሎች አገራዊ ስሜት የሌላቸው ዘረኞች ከመጋረጃው ጀርባ ያሉ የሰይጣን ልጆችን ነው የራሱ መሪ አድርጎ የሾማቸው እና “እናንተ እየመራችሁኝ” የሚለው። ሃ/ማሪያም ደሳለኝ የብዙሃን መሪነቱን ትቶ ፤ጥቂቶችን ለመከተል የመረጠ ስለሆነ ከእርሱና እርሱ ካለበት ድርጅት ነጻነትን፤ፍትህንና እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መጠበቅ አይቻልም። ኢሕአዴግ/ህወሃት ነፃነትን ሳያውቅ ስለነጻነት በባዶ የሚጮኽ፤የፍትህ ውብት ያልገባው ግን ደግሞ ስለፍትህ ከማንም በላይ ለማስተማር የሚሞክር፤ የዴሞክራሲን ዋጋ ሳያውቅ ዴሞክራሲን አመጣሁላችሁ ማለትን ብቻ የሚያውቅ ሃሰተኛ ድርጅት ነው። ህወሃትን ከውሸት፤ ውሸትን ከህወሃት መለየት የማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል።ህወሃት ወይም የመለስ ዜናዊ ደቀመዝሙራን በውሸት ዓለም ውስጥ የኖሩ የጭለማው ንጉሶች እንጂ ለኢትዮጵያችን በጎ ራዕይ ያላቸው አይደሉም።

የመለስን ራዕይ ማስፈፀም ማለት እኔ ብቻ ባይነትን፤ ሃሰተኝነትን፤ በዘር ላይ የተመሠረተውን አድልዎ፤የተጀመረውን የመሬት ንጥቂያ፤ ዜጎች በነፃነት እንዳያስቡ የሚደረገውን አፈና አስፋፍቶና አጉልቶ ማስፈፀም ማለት ነው እንጂ ሌላ በጎ ነገር የለም። መለስ ዜናዊ ከጨቅላነቱ ዘመናት ጀምሮ በጥላቻ ተኮትኩቶ ያደገ እንጂ በፍቅር ታንፆ ያደገ ሰው ባለመሆኑ ትቶት ያለፈውም ከቅምና ጥላቻ የጸዳ ነገር አይደለም። ገና ህፃን ሳለ የመሃል አገር ህዝብ በተለይም አማራ ጠላት እንደሆነ እየተነገረው ያደገ፤ ያንንም ህዝብ ለመበቀል በቂም ዕዳ አገሪቷንና ህዝቧን ዋጋ ሲያስከፍል ኖሮ ለይቅርታና ለንሰሃ ሳይታደል ያለፈ ግለሰብ ነው። መለስ ዜናዊ በህይወት ዘመኑ ከቀደሙት ነገስታት መካከል አፄ ቴዎድሮስንና አፄ ምንሊክን ሲያንቋሽሽ ብዙ ጊዜ ተደምጦአል። ”አፄ ቴዎድሮስን ሲከሳቸው ኢትዮጵያን አንድ ሊያደርጉ የሄዱበት መንገድ በጉልበት ስለነበር ኢትዮጵያን አንድ ሳያደርጉ አልፈዋል” ይል ነበር። የዚህ ዋና ዓላማ አፄ ቴዎድሮስን በማንቋሸሽ የእርሱን የረከሰ ስብዕና መገንባት ነበር። እርሱ በዚህ ዘመን በዚያች አገር ላይ እኔ ያልኩት ብቻ ካልሆነ ብሎ የገደላቸውን ዜጎች፤በእርሱ እምቢ ማለት አገራቸውን ትተው የተሰደዱ የአገሪቷን ዜጎች፤በርሱ ምክንያት በየእስር ቤቱ ታጉረው የሚሰቃዩ ዜጎችን በተመለከተ ግን የሚጠይቀው እንዳይኖር ማድረጉን ዜጎች የሚያውቁ አይመስለውም። ስለ አፄ ምንሊክ ክፋት ሲናገር ደግሞ “ቴክኖሎጂን ለማስፋፋት በውጭ አገር ሙያተኞች ላይ ማተኮራቸው አገሪቷን ለድህነት ዳርጓታል” ብሎ ነበር። የንጉሱ ድርጊት በፍጹም ሊያስመሰግናቸው የሚገባ ትልቅ ተግባር ቢሆንም መለስ ዜናዊ ግን ሊያራክሰው ሞክሯል። ይሄ አባባሉ የፍጹም ጥላቻው መገለጫ መሆኑን ከማሳየት በቀረ የፈየደው ቁም ነገር አልነበረም። አፄ ምንሊክ በዚያ ዘመን የመሠረቱትን ቴሌ ዛሬ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያዊያንን እየነቀለ ለውጭ አገራት ኩባኒያዎች ሰጥቷል። የሚያሳፍረውም አገርን ድሃ የሚያደርገውም የመለስ ዜናዊ ሥራ እንጂ የአፄ ምንሊክ በጎ ራዕይ አልነበረም። እንግዲህ ሌላው የመለስ ዜናዊ ራዕይ የአገሪቷን መሠረቶች ማፈርስና በፍራሹም ላይ የራሱን የተጠላ ስብዕና መገንባት ነበር።ይህን የመሰለውን ራዕይ “ሳልበርዝ ሳልከልስ” አስፈጽማለው ማለት ትልቅ ስህተት ነው። በታሪክም ያስወቅሳል።

የመለስ ዜናዊ ራዕይ በትግራይ ልጆች ግንባር ቀደም ተጋዳላይነት በተገኘው ድል ለርሱ ታማኝ የሆኑትን አባላቱን ልዩ ተጠቃሚ በማድረግ ከተቻለ ፓርቲው እስከ ወዲያኛው ትውልድ እንዲገዛ ማድረግ ነው። ለዚህም ስጋና ደማቸው እየተቆጠረ የኔ ነው የሚላቸውን ሁሉ የአገሪቱን ግዙፍ ተቋማት እንዲቆጣጠሩት ያደረገው። በተለይ እርቃኑን የወጣው በመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ ያለው ዘርን መሠረት ያደረገ አወቃቀር የመለስ ዜናዊ ዘረኝነት ደረጃ አመልካች እንጂ በአፍ ሲያወራና ተከታዮቹ እንደገደል ማሚቶ ተቀብለው ሲያስተጋቡት እንደኖሩት የብሄሮችን እኩልነት የሚያረጋግጥ አይደለም።የብሄሮችን እኩልነት አረጋግጣለው ብሎ ድምጹን ከፍ አድርጎ ጬኾ ሲያበቃ በብሄሮች መካከል በግልጽ የሚታይ አድልዎ የፈፀመ መለስ ዜናዊና እርሱ የሚመራው ህወሃት የተባለው ዘረኛ ድርጅት እንጂ ሌላ ማንም አይደለም።የመለስ ዜናዊ ራእይ ብዙሃኑ ኢትዮጵያዊያን ጥቂቶችን ተሸክመው፤ራሳቸውን “ወርቅ እና ጀግና” ብለው የሚጠሩ ጥቂቶች ደግሞ ብዙሃኑን ተጭነው እንዲኖሩ ነው። ሃይለማሪያም ደሳለኝ ይሄንን ራዕይ ነው እንግዲህ “ሳልበርዝ ሳልከልስ” አስፈፅማለው በማለት ደጋግሞ ቃል እየገባ ያለው ። ይህ ደግሞ ሌላው ቀርቶ ለራሱ ክብር አለኝ ከሚል ተራ ዜጋ ረንኳ የሚጠበቅ አይሆንም። እንዴት ሰው መርጦ ባልተወለደበት ዘሩ ምክንያት ስብዕናው ሲዋረድ ተሸክሞ ይኖራል? እንዴትስ ቢሆን ነው በውክልና የራሱን ስብዕና ያዋረደውን ፖሊሲ ሳይከለስ ሳይበረዝ እተገብራለሁ ብሎ ቃል የሚገባው? ይሄንን ጥያቄ ለመመለስ ሃይለማሪያም ደሳለኝን መሆን ይጠይቃል።

ነገሮችን ለማሳጠር መለስ ዜናዊ ለአገርና ለወገን የሚበጅ በጎ ራዕይ ያልነበረው ግለሰብ ነበር። ይሄን ሃቅ ወደጎን ትተው ”አባይን የደፈረ” የሚል ባዶ ጩኸት የሚጮሁለት ሁሉ ሊያስተውሉት የሚገባው ቁምነገር አባይን ለመገደብ ቅንነቱ ከነበረ ሱዳን አፍንጫ ሥር ሂዶ ድንጋይ ማስቀመጥ ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ሲባል የተፈጸመ አጉል ጀብደኝነት እንጂ ለአገር ከማሰብ የሚመነጭ አለመሆኑን የሚገነዘቡበት ቀን ሩቅ አይሆንም። ”አባይን የደፈረ” ከሚለው ባዶ ጩኸት ባሻገር አባይ ተገድቦ ለልማት ሲውል ማየት የሁላችንም የዘመናት ራዕይ ሆኖ የኖረ ነው። ለመለስ “አባይን የደፈረ” ተብሎ በካድሬዎቹና የጥቅም ተከታዮቹ የሚጮኸው ባዶ ጩኸት ምን እንደሆነ ለሰሚው ቀርቶ ለጯሂዎቹም ግልጽ አለመሆኑ ይፋ እየሆነ መጥቶአል። እንኳን የውጪውን የአገር ውስጡንም ችግር ለመቅረፍ ፈቃደኝነትና ቀናነት ሳይኖር ምንም አቅምና የገንዘብ ጉልበት ሳይኖር በባዶ ሜዳ ስለ አባይ መደስኮር ጀብደኛ ያሰኝ እንደሆን እንጂ የሚያስወድስና የሚያስሞካሽ አይደለም።

መለስ ዜናዊ ለዚያች አገር በጎ ራዕይ ያለው መሪ ቢሆን ኑሮ ባለፉት 21 ዓመታት ውስጥ የፈሰሰው ደም በኢትዮጵያች ምድር ባልፈሰሰ ነበር። ኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብትን ከሚረግጡ አገሮች ተርታ ባልተሰለፈች ነበር። እሥር ቤቶች በጋዜጠኞች እና በፖለቲካ ድርጅት አባላትና መሪዎች ባልተጨናነቁ ነበር። አገራችን ዘመኑ ከደረሰበት የኢንቴርኔትና የሳታላይት አገልግሎቶች ታግዳ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ኋላ ቀር ባልተባለች ነበር። ዜጎች ያለፍርሃት ሃሳባቸውን መግለጽ የሚችሉባት አገር በሆነች ነበር። የአገሪቱ አንጡራ ሃብት ለዘርፎ አስዘራፊ ክፍት ባልሆነ ነበር፤ ለም መሬታችን ከተወላጅ ተነጥቆ ለባዕዳን ባልተቸበቸበ ነበር። ኤረ ስንቱ ተዘርዝሮ ያልቃል? ታዲያ እነዚህ ቀላል ግን ደግሞ መሠረታዊ ጥያቄዎች መልስ ያላገኙባትን አገር ትቶ ያለፈ ግለሰብን ትልቅ ራዕይ ያለው መሪ አድርጎ መለፍለፍ ከትዝብት በቀር የሚጨምረው ነገር ከቶ ምን ይሆን?

እንግዲህ ሃ/ማሪያም ደሳለኝ በዚያች አገር ፈርጀ ብዙ ችግሮችን ፈጥሮ ያለፈውን የመለስ ዜናዊን ራዕይ ሳልበርዝ ሳልከልስ አስፈጽማለው ማለቱ ለአገራችን አይበጃትም። እርሱ ተመርጦ ሳይሆን በህወሃት ተመድቦ ነው ሥልጣን የያዘውና ከመጋረጃ በስተጀርባ ሆነው ሊያሽከረክሩት ከሾሙት ጥቂት የህወአት ማፊያዎች ጥቅም አስከባሪነት ያለፈ ተግባር ሊያከናውን ይችላል ተብሎ መታሰብ የለበትም። እናም እኛ ብዙሃን ያለን ብቸኛ አማራጭ ህወቶች ሃ/ማሪያም ደሳለኝንና መሰሎቹን አስከትለው ሊነፍጉን የሚሞክሩትን ነፃነታችንን ለማስመለስ ቀበቷችንን ጠበቅ አድርገን ግንባራችንን ሳናጥፍ የጀመርነውን ትግል መቀጠል ብቻ ነው።

ግንቦት ሰባት ለፍትህ፤ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ ለእኩልነት እና ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ግንባታ የጀመረውን ትግል አጠናክሮ ይቀጥላ። ከሌሎች የህግ የበላይነት ተመስርቶ፤ ምርጫ ቦርድ ገለልተኛ ሁኖ፤ የፀጥታውና የአገር መከላከያ ኃይሉ ከተያዘበት የዘረኝነት ሰንሰለት ተላቆ፤ ዜጎች በአመለካከታቸው ብቻ አሸባሪ መባላቸው ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ አብቅቶ፤ የሙያ ማህበራት ያለ መንግስት ጣልቃ ገብነት መደራጀት ችለው ለማየት ከምር ፍላጎት ካላቸው ድርጅቶች ጋርም የጀመረውን አብሮ የመታገል ስልት በረቀቀ ዜዴ አጠናክሮ ይቀጥልበታል።

በመጨረሻም እንዲህ ያለ ሥርዓት በኢትዮጵያ ተመሥርቶ ማየት የምትፈልጉ ሁሉ ከትግሉ ጎራ እንድትቀላቀሉ የትግል ጥሪያችንን እናቀርባለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ ራዕይ ሳይሸራረፍ እተገብራለሁ በማለት ቃል የገባው ሀይለማሪያም ደሳለኝ አወዛጋቢውን መሬት ለባዕዳን የመሸጥ ፖሊሲ እንደሚገፋበት አስታወቀ

ላለፉት አምስት አመታት የኢትዮጵያን ደሃ ገበሬ በጠመንጃ ኃይል እያፈናቀለ መሬቱን በርካሽ ለባዕዳን ሲቸበችብ የከረመዉ የወያኔ አገዛዝ አገር ዉስጥና ከአገር ዉጭ የተቀሰቀሰበትን ከፍተኛ ህዝባዊ ቁጣና ተቃዉሞ ጆሮ ዳባ ልብስ በማለት አሁንም ደሃዉን ገበሬ እያባረረ መሬት መሸጡን የሚቀጥል መሆኑን አስታወቀ።

ኃ/ማሪያም ደሳለኝ የራሱ የሆነ ራዕይ እንደሌለዉና ጥረቱ ሁሉ የጌታዉን የመለስ ዜናዊን ራዕይ ክግቡ ለማድረስ መሆኑን ደጋግሞ የተናገረ ቢሆንም መሬት ሽያጭን የመሰለ አጅግ አወዛጋቢ እርምጃ አንዲህ በአጭር ግዜ ይወስዳል የሚል ግምት በብዙዎች ዘንድ አልነበረም። ሆኖም የኃ/ማሪያም ደሳለኝ አገዛዝ መሬት የመሸጡን ፖሊሲ አሁንም እንገፋበታልን በማለት አገዛዙ የሚጨነቀዉ ለኢትዮጵያ ህዝብ ሳይሆን አሁንም የህወሀት ባለስልጣኖችንና የደጋፊዎቻቸዉን ኪስ ለመሙላት መሆኑን በተግባር እያሳየ ነዉ ሲሉ ብዙዎች ትችት በመሰንዘር ላይ ናቸዉ።

ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚካሄደዉን የመሬት ንጥቂያ በቅርብ የሚከታተሉ ምሁራንና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ባለፉት አመታት የተካሄደዉን የመሬት ሽያጭ አጥብቀዉ ሲቃወሙ የቆዩ ቢሆንም የወያኔ አገዛዝ ግን በያዝነዉ አመት አንድ መቶ ሺ ሄክታር መሬት ለባዕዳን ለመሸጥ ማቀዱን አስታዉቋል። የመሬት ሽያጩ የሚካሄደዉ በኦሮሚያ፤ በአማራ፤ በጋምቤላና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ሲሆን ከዚህ ቀደም በእነዚህ ክልሎች የተካሄደዉ የመሬት ሽያጭ ከፍተኛ ህዝባዊ ቁጣ መቀስቀሱና በተለይ ጋምቤላ ዉስጥ ህዝቡ ጫካ ገብቶ የትጥቅ ትግል እንዲጀምር ማድረጉ ይታወቃል።

ኢትዮጵያ ዉስጥ "የብሔር ብሄረሰቦች" እኩልነት ተከብሯል የሚለዉንና መለስ ዜናዊ ያስተማረዉን መዝሙር እንደ ዳዊት ከመድገም ዉጭ "መብት" ማለት ምን እንደሆነ የማያዉቀዉ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ የኢትዮጵያን ደሃ ገበሬ ከመሬቱ እያፈናቀለ መሬቱን ለመሸጥ መወሰኑ የሚያሳየን ነገር ቢሆን እሱም እንደ ጌታዉ እንደ መለስ ዜናዊ ለዜጎች የአገር ባለቤትነት መብት ምንም ደንታ የሌለው መሆኑን ገና ሥልጣን ላይ ሳይደላደል መግለጹ ለውጥ ሊኖር ይችላል ብለው የሚያስቡትን ወገኖች ቅስም የሰበረ መሆኑ ይገመታል።

ሃይለማሪያም ደሳለኝ "ዘላለማዊ ክብርና ሞገስ ለአምላካችን ይሁን" የሚለውን አምልኮአዊ አነጋገር ገልብጦ " ክብርና ሞገስ ለዘላለሙ ለታላቁ መሪያችን ይሁን ሲል መደመጡ መለስ ዜናዊ አሳርፎበት ከሄደው የበታቸኝነት ስሜት ገና ባለማገገም አምልኮ መለስ ጀምሮአል የሚል ትችት አስከትሎበታል።

## በኩማ ደመቅሳ የሚመራው የአዲስ አበባ አስተዳደር ከ1000 በላይ ዜጎችን የሚኖሩበትን መኖሪያ ቤት በማፍረስ ለጎዳና ተዳዳሪነት እንደዳረጋቸው ተዘገበ

በወያኔዉ ተላላኪ በኩማ ደመቅሳ የሚመራዉ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር በነፋስ ስልክ አካባቢ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ዉስጥ ካለፈዉ መስከረም 19 ቀን ጀምሮ የተያያዘዉ የመኖሪያ ቤት ማፍረስ ዘመቻ ቁጥራቸዉ ከአንድ ሺ በላይ የሚሆን ህፃናቶችን፤አሮጊቶችን፤ የሚያጠቡ እናቶችንና በህመም የሚሰቃዩ አረጋዉያንን ያለ መጠጊያ ባዶ ሜዳ ላይ ማስቀረቱን የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከልን ዜና ገለጸ።

የአዲስ አበባ መስተዳድር እንደዚህ አይነት ኢሰብዓዊ የሆነ የጭካኔ እርምጃ ሲወስድ ይህ የመጀመሪያዉ አለመሆኑን የገለጸዉ ዘጋቢያችን ህገወጥ ተብለዉ የፈረሱት አብዛኛዎቹ ቤቶች አገዛዙ እራሱ በጻፈዉ የድጋፍ ደብዳቤ ፈቃድ ተሰጥቶባቸውና አመታዊ ግብር እንዲከፍሉበት ሲደረግ የኖሩ መኖሪያ ቤቶችና ንግድ ድርጅቶች መሆናቸዉን ላፍቶ ክፍለ ከተማ ድረስ በመጓዝ ባደረገዉ ጥናት ማረጋገጥ ችሏል።

ከአዲስ አበባ በተለይ ከላፍቶ ክፍለ ከተማ በየቀኑ በሚደርሱን ዜናዎች መሠረት ክፍለ ከተማዋ በሚያለቅሱ ህፃናትና በህመም በሚሰቃዩ አረጋዉያን እንደተጥለቀለች ለማወቅ ተችሏል። የተፈናቃዮቹ ቤተሰቦች በየጎዳናዉ ተበትነዉ በሚገኙባቸዉ አካባቢዎች እየተዘዋወረ ሁኔታዉን የተከታተለዉ የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ከተፈናቃዮቹ መካከል ገና ከአራስ ቤት ያልወጡ መንታ የወለዱ እሜጫት ከህጻናት ልጆቻቸው ጋር በረንዳ ላይ ተጥለው በዝናብ ሲደበደቡ መመልከቱን ገልጾ በተለይ በምግብ እጥረትና በንጽህና ጉድለት አካባቢው ለተላላፊ በሽታ ሊጋለጥ እንደሚችል የተፈጠረው ስጋት ምንም ትኩረት አላገኘም ብሎአል።

ወያኔ የከተማ ቦታን በውድ ዋጋ ለባለሃብቶች በመቸብቸብ የጀመረው የሃብት ዘረፋ እጅግ ስለጣመው ዜጎችን በማፈናቀል ለሚፈጠረው ማህበራዊ ቀውስና ስቃይ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ኖሮአል። ሟቹን ዘረኛ አምባገነን መለስ ዜናዊን የተካው ሃይለማሪያም ደሳለኝ ይህንን የህዝብ መከራና ስቃይ ለማቃለል ፍላጎትም አቅምም እንደሌለው በአደባባይ እየሰጠው ካለው ቃል መረዳት ተችሎአል።

## የኢትዮጵያ መምህራን ለኃ/ማሪያም ደሳለኝ አመራር የታዛዥነት ቃል ኪዳናቸዉን እንዲያድሱና የመለስ ዜናዊን ራዕይ ተግባራዊ ለማድረግ በሚደረገዉ ትግል ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስገድድ የተሀድሶ ጉባኤ መዘጋጀቱ ታወቀ

የኢትዮጵያ መምህራን ወያኔ በተለምዶ "ተሀድሶ" እያለ በሚጠራዉ ጉባኤ ላይ እንዲሳተፉና በጉባኤዉ ላይ የመለስ ዜናዊን ራዕይ ለማስቀጠል ቃል እንዲገቡ የሚጠይቅ ደብዳቤ ለየትምህርት ቤቱ በመላክ ላይ መሆኑን ኢትዮጵያ ዉስጥ በየክልሉ የሚገኙ ምንጮቻችን ገለጹ።

ይህንን ለየትምህርት ቤቱ በመላክ ላይ ያለዉንና የተሀድሶ ፕሮግራሙን አስፈላጊነት የሚዘረዝረዉን ደብዳቤ እንደሚያስረዳው መምህራንና በትምህርቱ ዘርፍ የተሰማሩ ሰራተኞችን ተሀድሶ ፕሮግራም በማድረግ የመለስ ዜናዊን ራዕይ በመከተል የተጀመረውን የልማትና የመልካም አስተዳደር ተግባር በትምህርት ቤቶች ለማስፈንና ጅምሮችን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ቃል ኪዳን መግባት እንደሚኖርባቸው የሚያሳስብ ነው። ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ለተሀድሶ ጉበኤዉ ዝግጅት በነፍስ ወከፍ 600 ሺ ብር እንዲያዋጡ የሚጠይቅ መሆኑን ዘጋቢያችን በላከው ዜገባ ገልጿል።

የኢትዮጵያ መምህራን ላለፉት ሃያ አመታት በተከታታይ የጠየቁትን የመብትና የነፃነት ጥያቄ ረግጦና ህጋዊ ማህበራቸዉን አፍርሶ በራሱ ተለጣፊ ማህበር የተካዉ የወያኔ አገዛዝ ስለመለስ ዜናዊ ራዕይና ሰለ መልካም አስተዳደር ማዉራቱ ወያኔ ምን ያክል እብሪተኛና ማን አለብኝ አገዛዝ መሆኑን የሚያሳይ ነዉ ሲሉ ዘጋቢያችን ያናገራቸዉ ብዙ መምህራን በምሬት ተናግረዋል። ወያኔ የአገዛዝ ዕድሜውን ለማራዘም ትምህርት ቤቶችን የድጋፍ መሠረት ለማድር የጀመረውን ውጥን የአገዛዙ ቁንጮ መለስ ዜናዊ ከሞተም ቦኋላ መቀጠሉ ያስቆጣቸው አንዳንድ ለዘጋቢያችን አስተያየታቸውን የሰጡ መምህራን የአሁኑ የተሃዲሶ አላማ በኢህአደግ ድርጅቶች ውስጥ እየተፈጠረ ያለው መፈረካከስ ለመጠገን ሲባል በሁሉም ስፍራ ድጋፍ ለማሰባሰብ ለተለመደው አባል ምልመላና ፖለቲካ ሥልጠና ነው ።

## ትግሉን አጠናክሮ ከመቀጠል ውጪ አማራጭ የለም፤ለዚህ ደግሞ የተበታተኑ ተቃዋሚዎች በመሰባሰብ ጠንካራ ሀይል መፍጠር ይገባቸዋል ሲል በወያኔ የፈጠራ ሽብርተኝነት ክስ ተወንጅሎ በእስር ላይ የሚገኘው የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ከፍተኛ አመራር አንዱዓለም አራጌ አሳሰበ

እንደ ድርጅቱ የህዝብ ግንኙነት መግለጫ አንዱዓለም ይህን ያለው የመስቀልን በዓል ምክንያት በማድረግ ሊጠይቁት ወህኒ ቤት ለሄዱት የአንድነት ከፍተኛ አመራር አካላት ሲሆን በማያያዝም እኔ በማንም ላይ ክፉ ለማድረግ አስቤ አላውቅም፣ ይልቁንም ዓላማዬ ለሁሉም እኩል የሆነች ኢትዮጵያ እንድትኖር ማድረግ ነውና ሁሌም ፍጹም ሰላም ይሰማኛል ብሏል።

በማከልም ከዚህ በፊት እኔ በፍርድ ቤት መከራከር አልፈልግም ባልኩበት ወቅት ፓርቲዬ ለታሪክም ቢሆን ስለሚጠቅም ፍርድ ቤት ቀርበህ ተከራከር ባለኝ መሰረት ማድረጌን ጥሩሆኖ አግኝቼዋለሁ፤ እናም አሁንም ፓርቲዬ ይግባኝ እንድጠይቅ በወሰነው መሰረት ይግባኙ እንዲጀመር ተስማምቻለሁ በማለት ተናግሯል።

አመራሩም በበኩሉ ምንጊዜም ከጎኑ እንደሆነና ትግሉንም ግቡን እስኪመታ አጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጦለታል ያለው የድርጅቱ ህዝብ ግንኙነት መግለጫ ሊጠይቁት የሄዱት የአመራር አካላት እንደገለጹት በወቅቱ አንዱዓለም ከፍተኛ የመንፈስ ጥንካሬና የሞራል ልዕልና ይታይበት ነበር ማለታቸውን ጠቅሶአል።

አመራሩ አንዱዓለምን ለመጠየቅ ቃሊት በሄደበት ወቅት የእስር ቤቱ ሃላፊዎች አትገቡም ብሎ ለረጅም ሰዓታት እንዳንገላታቸው እነርሱም ያለመታከትና መሰልቸት መግባት እንዲችሉ ሲወተውቱ መዋላቸውን በመጨረሻም ከ6 ሰዓት ቦኋላ እንዲመጡ ሲነገራቸው እሺ ብለው በቀጥታ ወደ ቂሊንጦ እስር ቤት በመጓዝ ናትናኤል መኮንንን ጠይቆ እንደተመለሱ የህዝብግንኙነቱ መግለጫ አስረድቷል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org